# ዳይናሚክ
## መሠረታዊ

**አንድ - ለአንድ**

Dynamic Churches
International

## መታሰቢያነቱ

ይህ የስልጠና መጽሐፍ በምድር ላይ ያለ ማንኛውም ሰው እግዚአብሔርን በግሉ ለማወቅ አጋጣሚውን /እድሉን/ እስኪያገኝ ድረስ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለመመስከር እና ሌሎችም እንደዚሁ ተመሳሳይ ስራ እንዲሰሩ ለማሰልጠን ራሳቸውን ለሰጡ ሁሉ መታሰቢያ ሆኗል፡፡

## ምስጋና

ይህ የስልጠና መጽሐፍ እያንዳንዱ ክርስትያን ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ምልልስ እንዲያድግና ለሌሎች የተማረውን ነገር ማስተላለፍ እንዲችል የተመረጠ መረጃ እንዲሰጥ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡ ለዚህ መጽሐፍ መጎልበት መረዳታቸውን አስተዋፅኦ ላደረጉ ሰዎች ሁሉ ምስጋናችን ከፍ ያለ ነው፡፡

***«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል፡፡»*** 2ቆሮንቶስ 5÷17


***Dynamic Churches International***
**Canadian Address:**
164 Stonegate Close
Airdrie, Alberta T4B 2V2
(403)912-4438
info@dynamicchurches.org
www.dynamicchurches.org


እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡


Copyright © 2007 Dynamic Churches International
All rights reserved including translation

## ማውጫ


| | | ገፅ |
|---|---|---|
| 1. | በክርስቶስ የሆነ አዲስ ሕይወት | 1 |
| 2. | በድል የሆነ አዲስ ህይወት | 5 |
| 3. | በሐይል የታጀበ አዲስ ሕይወት<br>• የህይወት ታሪኬ ቅፅ | 9 |
| 4. | ሚዛናዊ አዲስ ሕይወት<br>ጠቅላላ መመሪያ ለመሪዎች | 15 |
| 5. | ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ - አንድ መልካም እድል | 19 |
| 6. | የዳይናሚክ መሰረታዊ የመሪዎች መምሪያ | 21 |
| 7. | የምስክር ወረቀት | |

# ዳይናሚክ

## መሠረታዊ

ክፍል 1

**በክርስቶስ የተገኘ አዲስ ሕይወት**

ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ መቀበልህ በዚህ ምድር ይሁን በሰማይ ለሚኖርህ አስደሳች ሕይወት አስደናቂ አቅምን የሚሰጥህ የዘለአለም ግንኙነት ጅማሬ ነው፡፡

በዚህ ክፍል፡-
1. የዘላለም ሕይወት ማለት ምን እንደሆነ
2. ኢየሱስን በግል የማወቁ ጠቀሜታ
3. የክርስቶስ ኢየሱስ ስለመሆንህ እርግጠኛ ስለምትሆንበት መንገድ

### 1. የዘላለም ሕይወት እግዚአብሔርን በግል ማወቅ ነው፡፡

*«እውነተኛ አምላክ የሆንኸውን አንተንና የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቅ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት፡፡»*

*ዮሐንስ 17÷3*

**«የዘላለም ሕይወት»** ረጅም ዘመን ከመኖር ላቅ ያለ ነው፤ እርሱ ጠቅላላ አዲስ ሕይወት ነው - ምንም አይነት ውስንነት የሌለበት እግዚአብሔራዊ ሕይወት ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በሚወደደው ሰው ማንነት ላይ አይወሰንም፡፡

ዮሐንስ 3÷16 እንዲህ ይላል፣ ***«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልናና፤ »***

እንደዚሁ ሁሉ እርሱ በታጋሽነቱ፣ በመልካምነቱና በይቅርባይነቱ ወይም በማንኛውም መንገድ ውሱን አይደለም፡፡

**«የዘላለም ሕይወት»** ማግኘት ማለት ሙሉ እና ትርጉም ያለው ህይወት ለመኖር እድሉን አገኘህ ማለት ነው፡፡

ወደዚህ የአዲስ ሕይወት ሙላት የመግባትህ ጥቅሞች ምንድን ናቸው?



### 2. ኢየሱስን በግል የማወቁ ጥቅሞች

እያንዳንዱን ጥቅስ አንብብና ከተስማሚው ሀሳብ ጋር አዛምድ (በነጠብጣብ አገናኝ)

| ጥቅስ | እግዚአብሔር ለእኔ ምን አደረገ | እንዴት ነው የተጠቀምኩት |
|---|---|---|
| ሮሜ 5÷8 | እግዚአብሔር ፍቅሩን አሳየኝ | አሮጌው ነገር አልፎ አዲሱ ነገር መጣ |
| ቆላስያስ 1÷13-14 | እግዚአብሔር ከጨለማው መንግስት ነፃ አውጣኝ | ባለኝ ነገር ረክቼ መኖር እችላለሁ |
| 2ቆሮንቶስ 5÷17 | አዲስ ፍጥረት ነኝ | እንደ ኃጢያተኛ ክርስቶስ ለእኔ ሞተ |
| ራዕይ 3÷20 | ክርስቶስ ወደ ሕይወቴ ገባ | አልጠፋም |
| ዕብራውያን 13÷5 | ክርስቶስ ፈፅሞ አይተወኝም | ወደ ልጁ መንግስት አሸጋገረኝ |
| ዮሐንስ 10÷28 | ኢየሱስ የዘላለም ህይወት ስጠኝ | ወደ እግዚአብሔር አቀረበኝ |
| 1 ጴጥሮስ 3÷18 | ክርስቶስ ለእኔ ኃጥያት ሞተ | ከእርሱ ጋር ህብረት ማድረግ እችላለሁ |

እነዚህ ሁሉ በረከቶች የእግዚአብሔር ፍቅር ውጤቶች ሲሆኑ፤ በእርሱ ላይና እርሱ በሰራው ስራ ላይ እምነታችንን በማድረግ የተቀበልናቸው ናቸው፡፡

ኤፌሶን 2÷8-9ን ተመልከት እና ባዶ ቦታዎችን ሙላ፡፡

***«በ--------------፣ በ------------ ድናችኋልና፤ ይህም --------------------------***

***--------------  ነው እንጂ----------------- አይደለም፤***

***ማንም እንዳይመካ -------------  አይደለም»***

ድነት የሚገኘው እምነታችንን
(በትክክለኛው መልስ ላይ አስምርበት)

1. ልትሰራው በምትችለው ነገር በማድረግ ነው፡፡
2. ኢየሱስ ክርስቶስ በሰራው ስራ ላይ በማድረግ ነው፡፡
3. ቤተክርስቲያንህ እየሰራች ባለው ላይ በማድረግ ነው፡፡
4. ወላጆችህ እየሰሩ ባሉት ላይ በማድረግ ነው፡፡

**3. የኢየሱስ ክርስቶስ መሆንህን የምታውቅበት መንገድ**

ዮሐንስ 3፥16ን አንብብ
የእግዚአብሔር የመነሻ ሐሳብ ምን ነበር?____________________
ምንድነው ያደረገው? ____________________
ማነው የተጠቀመው? ____________________
ምንድነው የሚኖራቸው? ____________________
ራዕይ 3፥20ን አንብብ ____________________
በክርስቶስ ያለውን እምነት ብቸኛ የመግለጫ መንገድ ____________
____________________

የአንተ ኃላፊነት ምንድን ነው; ____________________

የእርሱ ኃላፊነት ምንድን ነው; ____________________

ክርስቶስን ወደ ህይወትህ ጋብዘሐል; አሁን የት ነው ያለው;
____________________

ስለ ደህንነትህ እርግጠኛ ካልሆንክ፣ በልብህ ሆንብለህና ወስነህ ክርስቶስን በመቀበል እርግጠኛ መሆን ትችላለህ፡፡

ይኸው የንስሐ ፀሎት፡-

> **«ጌታ ኢየሱስ፣ እኔ ኃጥያተኛና እራሴን ማዳን የማልችል ሰው ነኝ፡፡ ለኃጢያቴ በመስቀል ላይ ስለሞትክልኝ** አመስግንሃለሁ፡፡ አሁን አንተን ወደ ሕይወቴ በመጋበዝ እንደ ግል አዳኜ አድርጌ **እቀበልሃለሁ ኃጥያቴን ይቅር ስላልከኝና የዘላለም ሕይወት ስለ ሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ አሁን በህይወቴ ላይ እንድትገዛ እራሴን አሳልፌ እሰጥሃለሁ፤ ደግሞም በእኔ ውስጥ እንደወደድከው የአንተን ዘላለማዊ ህይወት እንደምትኖር አምናለሁ፡፡»**

ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወትህ አስገባህ? ________________



ከአንተ ጋር ካለው ግንኙነት አንፃር ክርስቶስ አሁን የትነው ያለው? ራዕይ 3፥20
____________________

በምን ስልጣን አወቅህ? ____________________
1 ዮሐንስ 5፥10-13 አንብብ

የዘላለም ህይወት የሚሰጥ ማን ነው? (ቁጥር 11) ________________

የዘላለም ህይወት ከየት ነው የሚገኘው? (ቁጥር 11) ________________

የዘላለም ህይወት ያለው ማን ነው? (ቁጥር 12) ________________

የዘላለም ህይወት የሌለው ማን ነው? (ቁጥር 12) ________________

____________________

እግዚአብሔር ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት አለማመን እግዚአብሔርን ________ማድረግ ነው፡፡ (ቁጥር 10ን ተመልከት) እርሱ ________ነውን?

( ትክክለኛ ያልሆኑትን ቃላት ለይተህ አውጣ፡፡)
***«በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እናንተ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ* (ተስፋ ታደርጉ ዘንድ፣ይሰማችሁ ዘንድ፣ትገምቱ ዘንድ፣ለእርሱ ትሰሩ አንድ፣ታውቁ ዘንድ) *ይህን እጽፍላችኋለሁ፤»*** (1ዮሐንስ 5፥13

የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ታውቃለህ? ____________________
**በራስህ ጊዜ**

1. በዮሐንስ 3፥1-8 ያለውን የኒቆዲሞስ ታሪክ አንብብ
2. የሚከተለውን ቁጥር በቃልህ ያዝ፡፡

***«ምስክርነቱም ይህ ነው፤ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት ያለው በልጁ ነው፡፡ ልጁ ያለው ህይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም፡፡»*** 1 ዮሐንስ 5፥11-12

ይህንን አዲስ ሕይወት እንዳልኖር ከሚያግዱኝ ነገሮች እንዴት ድልን ልቀዳጅ እችላለሁ? ይህንን በሚቀጥለው ክፍል እንነጋገራለን፡፡

የሚቀጥለው ክፍላችን በድል የሆነ **አዲስ ህይወት የሚል ነው፡፡**

ሰዓት ________________ ቦታ ____________ቀን ________
**በፀሎት መዘጋት**

# ዳይናሚክ

## መሠረታዊ

ክፍል 2

### በድል የታጀበ አዲስ ህይወት

1ዮሐንስ 5÷11-12ን ከልስ። ከአዕምሮህ በትክክል ከጠቀስህ በኋላ በምልክት አረጋግጥ።
እግዚአብሔር እንዳቀደው ኖረህ ከሆነ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አስገራሚ አቅም ያለው አዲስ ሕይወት ጀምረሃል፤ ይሁንና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ህብረት ኃጥያትን በመስራት የማቋረጡም አደጋ ይኖራል።

በዚህ ክፍል
1. ኃጥያት ምን እንደሆነ
2. ለምን ኃጥያት እንደምንሰራ
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጥያት መድኃኒት እንደሆነ
4. የእግዚአብሔርን የኃጥያት መድኃኒት እንዴት እንደምንወስድ እንነጋገራለን

#### 1. ኃጥያት ምንድን ነው

ኃጥያት እግዚአብሔር የሚፈልገውን በመቃወም እኔ የምፈልገውን ማድረግ ነው። ኃጥያት የአመፅ አመለካከት ነው። መዋሸት፣ ማጭበርበር ወ.ዘ.ተ የዚህ አመፅ ውጤት ወይም ፍሬ ናቸው።

ክርስቶስን ከመቀበልህ በፊት፣ ኃጥያት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት እንዳታደርግ ከልክሎሃል። ኤፌሶን 2÷1-5ን አንብብ።

የአንተ መንፈሳዊ ሁኔታ ምን ነበር? (ቁጥር 1) ____________________
ህይወትህን ይገዛ የነበረው ምን ነበር? (ቁጥር 2) ____________________
በፍጥረትህ ምን አይነት ሰው ነበርክ? (ቁጥር 3) ________________
አሁን በእግዚአብሔር ምህረት ክርስቶስን ተቀብለኃል፤ ምንድነው የሆንከው?(ቁጥር 4-5)

______________________________________________

በህይወታችን የነበሩት ኃጥያቶች ውጤቶች ምንድን ናቸው? እነዚህን ቁጥሮች አንብቡና ተወያዩባቸው

ሮሜ 6÷23 ሮሜ 2÷8-9 መዝሙር 66÷18 ዮሐንስ 8÷34



#### 2. ኃጥያት የምንሰራው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር እርሱን ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ የሚችል ነፃ ፍቃድ ሰጥቶናል። (ሮሜ 6÷12-13)። እንደ ክርስቲያን፣ ኃጥያት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ህብረት ያሰናክላል። ለማደግና እግዚአብሔር እንደሚያስበው ለማሰብ ጊዜ ይወስዳል። አዕምሮአችን መታደስ ያስፈልገዋል(ሮሜ 12÷1-2)

በሐጥያት መፈተንና ኃጥያት ለሁላችንም የተለመዱ ናቸው።
ሦስት በኃጥያት የምንፈተንባቸው ቦታዎች የትኞቹ ናቸው?

1ዮሐንስ 2÷15-16

______________________________________________

______________________________________________

በኃጥያት መፈተን ኃጥያት ነውን? ዕብራውያን 4÷15 ________________

______________________________________________

በኃጥያት መፈተን ኃጥያት ወደ መስራት እንዳይመራን ምን ማድረግ እንችላለን?
1 ቆሮንቶስ 10÷13______________________________________

______________________________________________

እግዚአብሔር በኃጥያት መፈተን የምታመልጥበትን መንገድ ለማዘጋጀት ምንድነው እያደረገ ያለው?
ፊልጵስዩስ 2÷13 ___________________________________

______________________________________________

ሮሜ 6÷1-2ን አንብብ። እንደ ክርስቲያን በኃጥያት የማንቀጥለው በምን ምክንያት ነው? ______________________________________

#### 3. ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጥያታችን የእግዚአብሔር መድኃኒት ነው።

የክርስቶስ ሞት አላማ፦
ሀ. እኛን ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ ነበር
ለ. ለኃጥያታችን ዋጋ ለመክፈል ነበር (1 ጴጥሮስ 3÷18)

የሚከተለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብብ

*«እናንተም በበደላችሁና የሥጋችሁን ኃጥያታዊ ባሕርይ ባለ መገረዝ ሙታን ሳላችሁ፣ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ሕያዋን አደረጋችሁ፤ ኃጢአታችንንም ሁሉ ይቅርአለን፤*

*ሲቃወመንና ሲፃረረን የነበረውን የዕዳ ፅሕፈት*
*ከነሕግጋቱ በመደምሰስ፣ በመስቀል ላይ ቸንክሮ*
*ከመንገድ አስወግደው። »*

**(ቆላስያስ 2÷13-14)**

ክርስቶስ የሞተው ለስንቶቹ ኃጢአቶችህ ነበር?

ቈላስይስ 2÷13፣14 (ከላይ) ________________________________

**"ሁሉ"** ማለት **"ሁሉ"** ማለት ነው - ያለፈ፣ የአሁንና የወደፊት ማለት ነው። አሁን ክርስቶስን ስለተቀበልህ ከጠቅላላው ኃጥያት ይቅርታን አግኝተሃል። እንዴት ነው ይቅር መባልህን ማወቅህ ህይወትህን የሚቀይረው?

______________________________________________________

______________________________________________________

**4. *ለኃጥያት የእግዚአብሔር መድኃኒት የመውሰኛ መንገድ።***

*ኢየሱስ ለኃጥያትህ በመስቀል ላይ በመሞቱ ምክንያት ፈፅሞ ይቅር እንደተባልክ አስታውስ፤ ይሁንና ከእግዚአብሔር ጋር በየቀኑ ህብረት ማድረግህን ለመለማመድና የሚታወቅ ማንኛውንም ኃጥያት መናዘዝ ያስፈልግሃል።*

*ኃጥያታችንን ብንናዘዝ ፣ ክርስቶስ ምን ያደርጋል?*

1 ዮሐንስ 1÷9 ________________________________________

*መናዘዝ ማለት ስለኃጥያትህ ከእግዚብሔር ጋር መስማማት ነው።*

*ሀ. ያ ኃጥያት እንደሆነ መስማማት*

*ለ. እግዚአብሔር አስቀድሞ ይቅርታን ስላዘጋጀ ማመስገን*

*ሐ. አመለካከትህን መቀየር (ንስሐ)*

*መ. መመለስህን እግዚአብሔር በሐይሉ እንዲያፀናው መፍቀድ*

*ሠ. ይቅር መባልህን እንደ እውነታ በእምነት መቀበልና ከበደለኝነት ነፃ የሆነ ሕይወት መኖር።*

*ኃጥያትህን ስትናዘዝና የእግዚአብሔርን ይቅርታ ስትቀበል፣ ኃጥያትን ድል በነሳ ሕይወት ትደሰታለህ።*



**በራስህ**

በህይወትህ እግዚአብሔርን የማያስደስቱትን ማናቸውንም ነገሮች በዝርዝር ለመመዝገብ በራስህ የተወሰነ ጊዜ ውሰድ። ያ ኃጥያት እንደሆነ በእግዚአብሔር ፊት ተቀበል። ከዝርዝሩ ባሻገር 1ዮሐንስ 1÷9ን ፃፍ። እነዚህን ሁሉ ኃጥያቶች ይቅር ያለህን እግዚአብሔርን አመስግን። ይቅር እንደተባለ ሰው አሁን በድልና በነፃነት ኑር።

1. *መዝሙር 32ን አንብብ።*
   *ዳዊት ኃጥያቱን እንዴት ነበር የተመለከተው?*

   *ከመናዘዙ በፊት ምን ነበር የተሰማው;*

   *ከተናዘዙ በኂላ ምን ነበር የተሰማው;*

2. *ሉቃስ 15÷11-32 አንብብ።*
   *እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር የህዝቡን ኃጥያት የሚመለከትበትን መንገድ እንዴት ገልፀው ያሳያሉ?*

3. *የሚከተለውን ቁጥር በአዕምሮህ ያዝ።*

   *«ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን፣ ከዐመፃ ሁሉ ሊያነፃን እርሱ ታማኝና ፃድቅ ነው።»* 1ዮሐንስ 1÷9

*ይህንን አዲስ ህይወት ለመኖር እንዴት ኃይል ላገኝ እችላለሁ?*

የሚቀጥለው ክፍላችን **በሐይል የታጀበ አዲስ ህይወት የሚል ነው።**

*ሰዓት*_________ *ቦታ* ______________*ቀን* ________________

***በፀሎት መዝጋት***

# ዳይናሚክ

## መሠረታዊ

ክፍል 3

### በኃይል የታጀበ አዲስ ሕይወት

1ዮሐንስ 1÷9ን ክልስ። በቃልህ ጥቅሱን ከጠቀስክ በኋላ ምልክት አድርግ።

የክርስትና ሕይወት፣ በእውነት በጣም አስገራሚ እና በሰዎች አቅም ሊኖር የማይቻል አስደናቂ ሕይወት ነው ። ነገር ግን ይህንን ሕይወት እንኖር ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተሰጥቶናል። ምን አይነት አስገራሚ ሕይወት ነው!

| |
|---|
| በዚህ ክፍል<br>1. እንደ አዲስ ፍጥረት ስላለህ አዲስ አቅም<br>2. ስለአዲሱ የኃይልህ ምንጭ - መንፈስ ቅዱስ<br>3. በመንፈስ ቅዱስ ስለመመራት እና በኃይል ስለመታጠቂያ መንገድ እንነጋገራለን ። |

1. እንደ አዲስ ፍጥረት ያለህ አዲሱ አቅም

2ቆሮንቶስ 5÷17ን አንብብ።እንደ አዲስ ፍጥረት ምንድነው አልፎ የሄደው?

______________________________

በህይወትህ አልፈው የሄዱትን የተወሰኑ አመለካከቶችና ድርጊቶች ዘርዝር።

______________________________

በህይወትህ ያየኸው አዲስ ለውጥ ምንድን ነው?

______________________________

እነዚህ ሁሉ ለውጦች አዲስ ፍጥረት ስለመሆንህ ማስረጃዎች ናቸው። ከኃጥያት ኃይል ነፃ ወጥተኃል፣ ምክንያቱም አሮጌው ኃጥያት ወዳድ ፍጥረትህ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሏል።
ሮሜ 6÷6-7ን አንብብ።

የተሰቀለው ለምን ነበር? ______________________________

መቼ? ______________________________

ለምን? ______________________________



ሮሜ 6÷11-13ን አንብብ። አሁን ህይወታችንን መቆጠር የሚገባን እንዴት ነው? (ቁጥር)
11______________________ እና ____________________

2. መንፈስ ቅዱስ - የአንተ አዲሱ የኃይል ምንጭ

ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ ስትቀበል እግዚአብሔር የሆነው (1ቆሮንቶስ 2÷11-12) መንፈስ ቅድስ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ያትመዋል (ኤፌሶን 1÷13)፤ እናም ለዘላለም ከአንተ ጋር ይሆናል (ዮሐንስ 14÷16-17) ።

**መንፈስ ቅዱስ የመጣው ለምንድን ነው?**

ቁጥሮቹን ካነበብክ በኋላ ከትክክለኛው የመፅሐፍ ቅዱስ መረጃው ጋር አዛምድ።

| | | |
|---|---|---|
| ______ | ዮሐንስ 16÷8 | ሀ. ወደ እውነት ሁሉ ሊመራንና ሊመጣ ስላለው ሊያሳየን |
| ______ | ዮሐንስ 16÷13 | ለ. ኢየሱስን ሊያከብር |
| ______ | ዮሐንስ 16÷14 | ሐ. መመስከር እንችል ዘንድ ኃይልን ሊሰጠን |
| ______ | ሮሜ 8÷16 | መ. ዓለምን ስለኃጥያት፣ ፅድቅና ፍርድ ሊወቅስ |
| ______ | የሐዋርያት ስራ 1÷8 | ሠ. ልጆቹ እንደሆንን ሊያረጋግጥ። |

ምስክርነት ምንድን ነው? ______________________________

______________________________

ምን አይነት ፍሬ (መልካም ባህሪይ) መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ያፈራል?

ገላቲያ5÷22-23 ______________________________

በህይወትህ እነኚህ መልካም ባህሪያት እንዲኖሩ ትመኛለህ?

ማድረግ ያለብህ ምንድን ነው? ዮሐንስ5÷4-5 ____________________

______________________________


***መንፈሳዊ ህይወትህን ገምግም***

***ክርስቲያን ያልሆኑ*** **-** 1ቆሮንቶስ 2÷14፡፡ እነዚህ የክርስቶስን ሞት ለኃጥያታቸው እንደ ክፍያ አድርገው የማያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡

***ስጋዊ ክርስቲያን*** **-** 1ቆሮንቶስ 3÷1-2 እነዚህ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉ ሰዎች ናቸው፤ ነገርግን በስጋ ኃይል እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አይኖሩም፡፡


***መንፈሳዊ ክርስቲያን*** **-** 1ቆሮንቶስ 2÷15፡፡ እነዚህ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው የተቀበሉና መንፈስ ቅዱስ በኃይል ይሞላቸው ዘንድ የሚፈቅዱ ናቸው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሚመላለሱ ናቸው፡፡

**እ** - እኔነት እየተቆጣጠረ ነው
**ክ**-ክርስቶስ ከዚህ ህይወት ውጪ ነው





**በእኔነት የሚመራ**

**እ** - እኔነት እየተቆጣጠረ ነው
**ክ -** ክርስቶስ በዚህ ህይወት ቢኖርም ቾል የተባለና እንዲመራ አልተፈቀደለትም




**በእኔነት - የሚመራ**

**ክ -** ክርስቶስ በዚህ ህይወት እየኖረ እየተቆጣጠረ ነው
**እ -** እኔነት ለክርስቶስ ፍቃድ ራሱን አሳልፎ እየሰጠና መንፈስ ቅዱስ የመንፈስ ፍሬዎችን እያፈራ ነው




**በክርስቶስ - የሚመራ**

**የትኛው ክብ አሁን ያለህበትን ህይወት በተሻለ ይገልፃል?**

**3. በመንፈስ ቅዱስ ለመመራትና በኃይል ለመሞላት**

ሀ. ማንኛውንም የሚታወቅ ኃጥያት መናዘዝ (መዝሙር 66÷18)

ለ. እያንዳንዱን የህይወትክፍል ለክርስቶስ ማስገዛት(ሮሜ6÷12-13)

ሐ. መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህና በኃይል እንዲሞላህ መጠየቅ

በመንፈስ መሞላታችን የእግዚአብሔር ፍቃድ እንደሆነ እናውቃለን፤ ምክንያቱም እንድንሞላ አዞናል፡፡
(እንዲመራህና በኃይል እንዲሞላህ)



***« በመንፈስ ተሞሉ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ፣ ይህ ብክነት ነው»*** ኤፌሶን 5÷18

መ. በእምነት የተስፋ ቃሉን መቀበል፡፡
እንደ ፍቃዱ የሆነን ፀሎት እንደሚመልስ ተናግሯል፡፡
1 ዮሐንስ 5÷14-15ን አንብብ፡፡
በመንፈስ ቅዱስ መመራትህ የእግዚአብሔር ፍቃድ ነውን? __________
እርሱ እንዲመራህ ብትጠይቀው፣ ይመራሃልን? ____________________
እንዴት አወቅህ? ____________________________________________

በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ህይወት መኖር ማለት በእምነት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከክርስቶስ ጋር መለኮታዊ ህይወት መኖር ማለት ነው፡፡

ይህ ፀሎት እግዚአብሔር ህይወትህን እንዲመራ በእምነት የምትጠይቅበት አንድ መንገድ ነው፡፡

***«ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ የራሴን ህይወት በእራሴ እየመራው አንተን በድያለሁ፡፡ ኃጥያቴን ይቅር ስላልከኝ አመሰግንሃለሁ፡፡ አሁን ህይወቴን በጠቅላላ እንድትቆጣጠር እጠይቃለሁ፣ አሁን በእምነት የመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪቱን እቀበላለሁ፡፡ ስለምሪትህ አመሰግንሃለሁ፡፡»***

መንፈስ ቅዱስ በኃይል እንዲሞላህ ጠይቀኸው ነበር? ____________________
አሁን በዚህ ጊዜ ሕይወትህን ተቆጣጥሮት እንዳለ ታምናለህ? ____________
እንዴት አወቅህ? ____________________________________________

**በራስህ**

1. በዚህ ሳምንት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደተሞላ ሰው በእምነት ተመላለስ፡፡ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር የሆንክባቸውን ጊዜ ተመልከት፡፡ ይህንን ካደረግህ በዚህ ትምህርት ነጥብ 3ን ተግባራዊ አድርግና የመንፈስ ቅዱስ አመራርን መቀበልህን ቀጥል፡፡
2. ከአሰልጣኝህ ጋር በሚቀጥለው ክፍለ ግዜ እንዴት በግልህ እግዚአብሔርን ወደማወቅ እንደመጣህ ለማካፈል ተዘጋጅ፡፡ የህይወት ታሪኬን መናገር የሚለውን የመስሪያ ወረቀት ተጠቀም፡፡
3. የሚከተለውን ቁጥር በአዕምሮህ ያዝ፡፡
***«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል፡፡»*** 2ቆሮንቶስ 5÷17

እንዴት ነው በክርስትና ሕይወታችን ሚዛናዊ የምንሆነው? የሚቀጥለው ክፍል ሚዛናዊ የሆነ አዲስ ህይወት በሚል ነው፡፡

ሰዓት ________________ ቦታ __________________ ቀን ________________
***በፀሎት መዝጋት***
***የህይወት ታሪኬን መናገር***

ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ተቀብለሃል። እግዚአብሔር በተለየ ሁኔታ በህይወትህ እየሰራ ነው። ለጓደኞችህ ታሪክህን መናገር ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት አስደናቂ መንገድ ነው። የሚሰሙህ ሰዎች እነርሱም እርሱን ለማወቅ እንዲጓጉና በግል እርሱን መቀበል ምን መሆኑን ያውቁ ዘንድ፣ ታሪክህን ግልፅና የሚማርክ ግን ደግሞ ቀላል ማድረግ ይኖርብሃል።

**የህይወት ታሪክህን ለማዘጋጀት የሚረዱ ጥቂት ኃሳቦች**

1. በምትፅፍበት ጊዜ እግዚአብሔር ምሪት እንዲሰጥህ ፀልይ (ያዕቆብ 1÷5-6)
2. በብዙ ቃላቶች አትዘብዝብ፤ ማለት የፈለከውን ብቻ ተናገር ወይም እንዴት መጥፎ ህይወት እንደነበረህ አጠንክረህ ተናገር።
3. ሌሎች ከአንተ ያለፉ ወይም የአሁን ልምምዶችህ ውስጥ አብረውህ እንዲሆኑ እንዲሰማቸው አድርገህ ፃፈው። ስለአመለካከት ለውጦችህ አውራ እነርሱም ከጥላቻ ወደ ፍቅር፣ ከጭንቀት ወደ ደስታ፣ ከስጋት ወደ ሰላም ካለመታገስ ወደ መታገስ ከስርዓት አልበኝነ ወደ ሰላማዊ ሰውነት እንደመጣህ
4. የክርስትና ህይወት ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለበት አድርገህ በመናገር በሰዎች ላይ ተፅዕኖ አታድርግ።
5. ከመጨረሻው ረቂቅ በፊት በጥንቃቄ አርመው፤ እንደ አስፈላጊነቱም ደግመህ ፃፍ።
6. ምስክርነትህን በማስታወስና፣ በመለማመድ ከአንተ ጋር እስኪዋሃድ ድረስ በአዕምሮህ ያዘው።
7. ከዚህ በታች ያሉትን አራት ዋና ዋና ሐሳቦች በማጥናት የህይወት ታሪኬን መናገር የመስሪያ ገፅ ላይ ታሪክህን ፃፍ።

**ክርስቶስን ከመቀበሌ በፊት የነበረኝ ሕይወት**

- አስታውስ፣ የምትናገረው ያለኸው ክርስቶስን ለማያውቁ ሰዎች ነው። ከልምምድህ ጋር ያገናኙታል? የህይወት ታሪክህ እውነት ነው?
- ኢየሱስ ክርስቶስን ከመቀበልህ በፊት የነበረህን ህይወት ግለፅ።
- ክርስቶስን እንድትቀበል ያነሳሳህ ምን ነበር?

**እንዴት ክርስቶስን እንደተቀበልኩ**

- እንዴት ነበር ክርስቶስ ኢየሱስን ወደ ህይወትህ የጋበዝከው?
- ታሪክህን ከመስማቱ የተነሳ አንድ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበል እንዴት እንደሆነና ለመቀበል የሚፈልግ መሆን ይኖርበታል። ይሄ በጣም ግልፅ መሆኑን አረጋግጥ!

**ክርስቶስን ከተቀበልኩ በኋላ ያለው ህይወቴ**

- እርሱ በህይወትህ የሰራውን አዎንታዊ ለውጦች ቀላልና ግልፅ ማሳያዎች ተጠቀም
  - ክርስቶስ ለአንተ ምን ማለት ነው?
  - ማሳያዎችህ እውነት ሊሆኑ ይገባቸዋል። ማንም ፍፁም እንዳይደለ አስታውስ።
  - በህይወትህ ልዩነትን ያመጣው ክርስቶስ እንደሆነ አሳይ።

**ተስማሚ የመፅሐፍ ቅዱስ ቁጥር**

ለእግዚአብሔር ያለህን አድናቆት የሚገልፅና ሕይወቱን በማካፈል በህይወትህ እየሰራ ስላለውና ስለሚመጣው አዲስ ተስፋ ጥቅስ ምረጥ።

**ታሪክህን ስትናገር ይህን አረጋግጥ።**

- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ከልብህና በጋለ ፍላጐት ማካፈልህን። (ኤፌሶን 5÷8)
- ፈገግ በል! እግዚአብሔር ደስተኛና የሚያበራ ፊት እንዲሰጥህጠይቀው!



**የህይወቴ ታሪኬ የመስሪያ ቅፅ**

**ክርስቶስን ከመቀበሌ በፊት ያለው ህይወቴ፡-**

**እንዴት ክርስቶስን እንደተቀበልኩ፡-**

**ክርስቶስን ከተቀበልኩ በኋላ ያለው ህይወቴ፡-**

**ተስማሚ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ፡-**

# ዳይናሚክ


## --መሠረታዊ--

ክፍል 4

**ሚዛናዊነትን የጠበቀ አዲስ ህይወት**

2ቆሮ 5÷17ን ከልስ። በትክክል ከጠቀስከው በኂላ በምልክት አረጋግጥ _______ **የህይወት ታሪኬን** ለአሰልጣኙ ማካፈልና እንዳስፈላጊነቱ መከለስ።

**ግንኙነት**




ትርጉም ያለው የእርስ በእርስ ግንኙነት ለማጐልበት ግንኙነት ወሳኝ ነው። እንደ ክርስቲያን ሚዛናዊ ህይወት እንኖር ዘንድ በኃይል የሚያስታጥቀን መንፈስ ቅዱስ አለን።

በዚህ ክፍል እንዴት ሚዛናዊ ህይወት እንደምንኖር እንማራለን

1. እግዚአብሔርን በምስጋና እና በፀሎት ስናመልከው
2. ከመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ከእግዚአብሔር ስንማር
3. ህብረት ስናደርግና በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ስናድግ።
4. ያገኘነውን አዲስ ህይወት ለሌሎች ስናካፍል።

### 1. እግዚአብሔርን በምስጋና እና በፀሎት ማምለክ

እግዚአብሔርን ማምለክ ማለት እግዚአብሔር በህይወታችን ከማንም ወይም ከምንም ነገር በላይ እንደሚበልጥብን እውቅና መስጠት ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ብቻ አምልኮ የተገባው ነው።

**ምስጋና**

እግዚአብሔር በሕዝቡ ምስጋና ይደሰታል።

መዝ 33÷1-3ን አንብብ። እነዚህ ቁጥሮች ስለምስጋና ምን ይናገራሉ?

_______________________________________________

አፅናፈ አለሙ የእግዚአሔርን ታላቅነት ያውጃል።
ለምንድነው የምናመልከው?

ኤፌሶን 1÷3 _______________________________________



**ፀሎት**

እግዚአብሔርን መጠየቅ የሚኖርብን ስለምን አይነት ነገሮች ነው?

ፊልጵሲዩስ 4÷6 _______________________________________

ለምንድነው ምስጋና ማቅረብ አስፈላጊ የሆነው? ____________________

እግዚአብሔር በምንም ነገር እንድንሰጋ አይፈልግም። ለእኛ ያለው መሻት ምንድን ነው?
ፊልጵሲዩስ 4÷7 _______________________________________

በዮሐንስ 16÷24 መሰረት የፀሎት ዓላማ ምንድን ነው? ______________

_______________________________________________

እግዚአብሔር ይወድሃል - የእርሱ ልጅ ነህ። በሚያሳስብህ ነገር ሁሉ ወደ እርሱ እንድትመጣ ይፈልጋል።

በዚህ ግዜ በአንድ ላይ የምንፀልይበት ጉዳይ ይኖራል?

እስቲ ቆም ብለን ስለሚያሳስበን ነገር እንፀልይ። እስቲ እርሱን በማንነቱ በማመስገን እንጀምር።

### 2. በመፅሐፍ ቅድስ ጥናት ከእግዚአብሔር መማር

እንደማንኛው አፍቃሪ አባት እግዚአብሔር ከእርሱ እንድንማር ይፈልጋል። መንገዶቹ ከእኛ መንገዶች በጣም የራቁ ስለሆኑ ሐሳቦቹን ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። ጊዜንና ጥረትን ይጠይቃል።

ሮሜ 12÷2ን አንብብ።

ምንድነው መሆን የሌለብን? ______________________________
ምንድነው መሆን ያለብን? _______________________________
እንዴት? _____________________________________________
ውጤቱ ምን ይሆናል? ___________________________________
_______________________________________________

ያ ያንተ ምኞት ነውን?_____________

የእግዚአብሔር ቃል፣ መፅሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን እውነት እንድናስብ አዕምሮአችንን የምናድስበት የእርሱ መመሪያ ነው።

2ጢሞቲዎስ 3፥16-17ን አንብብ። መፅሐፍ ቅዱስን በማጥናት የሚገኙትን አራት ጥቅሞች ግለፅ።

1. ______________________ 2.. ______________________
3. ______________________ 4. ______________________

መፅሐፍ ቅዱስን በየዕለቱ ለማንበብና ለማጥናት ትፈልግ ይሆናል። ዛሬ በእያንዳንዱ ቀን አንድ ምዕራፍ ከዮሐንስ ወንጌል ለማንበብ ጀምር።

**3. ህብረት በማድረግ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ማደግ።**

እግዚአብሔር ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር እንደ ቤተሰብ አካል ህብረት በማድረግ እንድንደሰት ይፈልጋል።

ዕብራውያን 10፥24-25 ______________________________

______________________________ይላል።

ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር በመሆን እንዴት ነው ተጠቃሚ የምትሆነው? __

______________________________

እስከአሁን ካልጀመርክ፣ በመፅሀፍ ቅዱስ ወደምታምን ጤናማ ቤተክርስቲያን ወይም ወደ ህይወት ቡድን በመሄድ መጀመር ይኖርብሃል። ይህ ለአንተ እውነተኛ መበረታታት ይሆናል።

**አብሮ ማደግ**

በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ለማደግ ቀጣዩን ደረጃ ውሰድ። እስካሁን እንደዚያ ለማድረግ ያልጀመርክ ከሆነ፣ በዚህ ሳምንት አንድ ጓደኛህን በዳይናሚክ መሠረታዊ ማሰልጠንን ጀምር። ደግሞም ወደ አንድ ለአንድ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግን ለመቀጠል ዕቅድ ማውጣት። አንድ ሰው ከአንተ ጋር ለመገናኘት ይገኛል።

ለምንድነው ትጉህ መሆን ያለብን? 2ጢሞቲያስ 2፥15። ይህንን ቁጥር ፃፍ።

______________________________

______________________________

______________________________



## 4. ያገኘኸውን ህይወት ለሌሎች ማካፍል

አሁን ላንተ የሆኑትን መልካም ነገሮች ለመረዳት ጅማሬ ላይ ነው ያለኸው። እስካአሁን የተለማመድካቸው ለውጦች ምንድን ናቸው?

______________________________

ቤተሰቦችህና ጓደኞችህ ደስ የሚሰኙባቸው ለውጦች ናቸው? __________

ክርስቶስን በማወቅ የሚገኘውን ደስታ መለማመድ ከመቻላቸው ባሻገር ለምን ሌላ ነገር መካፈል ያስፈልጋቸዋል?
የሐዋርያት ስራ 4፥12 ______________________________

ከምን ሁኔታዎች ነው የዳነው? ______________________________

ክርስቶስን ከተከተልክ፣ ለአንተ ምን ያደርግልሃል?

ማርቆስ 1፥17 ______________________________

ለአንድ ጓደኛህ ታካፍል ዘንድ የህይወት ታሪኬን ማካፈልን አዘጋጅተኃል። ክርስቶስን እንዴት እንደተቀበልክ ለመናገርና ህይወትህን እንዴት እንደባረከው ለመናገር ምን አይነት ጓደኞችን እኔና አንተ መገናኘት ይኖርብናል።

ከ ______________ ለመገናኘት እወዳለሁ። መቼ? ______________
ጓደኛህ ክርስቶስን ቢቀበል፣ ከዛ በኋላ ዳይናሚክ መሠረታዊ እንዲጀምር ልንጋብዘው እንችላለን። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን እውነት መማር ይጀምሩ ዘንድ የህይወት ቡድናችን ወይም በቤተክርስቲያናችን እንዲካፈሉ መጋበዝ። አስታውስ አንተን ለመርዳት ከጎንህ እሆናለሁ።

ስለ አንድ ለአንድ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ መነጋገርና ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ - አንድ እድል የተሰኘውን ክፍል በሙሉ ማንበብና በአንድ ለአንድ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ለመቀጠል እርግጠኛ ሁን ነገር ግን ወደዚህ ስልጠና ከመሄድህ በፊት አንድን ሰው በዳይናሚክ መሠረታዊ ማሰልጠን መጀመር በጣም አስፈላጊ ነው።

የሚከተለውን ቁጥር በቃልህ ያዝ።

> ***«እንደማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል***
> ***እንደሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ፣ ራስህን***
> ***በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ።»*** 2ጢሞቴዎስ 2፥15

**በፀሎት መዝጋት**

# ዳይናሚክ

## *ደቀመዝሙር ማድረግ*

አንድ ለአንድ

**አንድ እድል**

በርካታ ክርስቲያኖች በአዲስ ኪዳን መልዕክቶች ውስጥ የሚገኙትን አይነት መለኮታዊ፣ በሐይል የታጀበና ሙሉ ህይወት ለመለማመድ ይፈልጋሉ፡፡ለእነርሱ ዝም ብሎ ትያትር መስራት አልነበረም፣ ነገር ግን እነርሱ «***ክርስቶስ በእኛ ሲኖር***» ብለው በሚገልጹት፣ በአዲስ የሕይወት ጥራት ሕይወታቸውን ማስወረር ነበር፡፡ለእግዚአብሔር ቃል ምላሽ ብንሰጥ፣ ያ አይነት ህይወት ለእኛም ይሆናል፡፡

ይህንን አዲስ የሕይወት ጥራት መለማመድ በቀጥታ ለእግዚአብሔር ቃል ካለን ምላሽ ጋር ይገናኛል፤ ኢየሱስ ለቃሉ ምላሽ የሰጡትን ሰዎች በአራት መንገድ ገልፃቸዋል፡፡ ማቴዎስ 13÷3-9 እና ከ18-23 አንብብ፡፡

የትኛው አፈር ነው ያንተን ህይወት የሚወክለው?

ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ቋሚ እድገት እንድታጎለበት ለመርዳትና ለአንድ ሌላ ሰው እንዴት እንደምታስተላልፍ ለማስተማር ጥሩ እድል ነው፡፡

***ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ምንድን ነው?***

1. ለእግዚአብሔርና ለሰዎች ሳለህ ህይወት እንድታድግ ለመርዳት /ለማገዝ/ በስነ-ስርዓቱ የተዘጋጀ ነው፡፡

2. በአንድ ሰው ሌላን ሰው (እርሱም ሌላን ሰው የሚያሰለጥን) ለማሰልጠን የሚጠቀምበት ዘጠኝ የአንድ ለአንድ የስልጠና ክፍለ ጊዜዎችን ይዟል፡፡

3. በሳምንት አንድ ጊዜ ለአንድ ሰዓት ተኩል ለመካፈል፣ መፅሐፍ ቅዱስ መርህዎችን ለመካፈል ለማጥናትና በአንድነት ለመፀለይ እንገኛለን፡፡

***ለምን አንድ ለአንድ መሆን አስፈለገ?***

1. የአጭር ጊዜ የአንድ ለአንድ ደቀመዝሙርነትን በቀላሉ የሚባዛ ነው፡፡ (ስልጠናን ወደ ሌላ ሰው ለማስተላለፍ በጣም ውጤታማ መንገድ)

2. ማንም ሰው ማለት ይቻላል አንድን ሰው ማሰልጠን ይችላል፡፡ አንድ ወንድ አንድ ሌላ ወንድ ያሰለጥናል፤ አንድ ሴት ሌላ አንዲት ሴትን ታሰለጥናለች፡፡



3. አንድ መሪን ለማጐልበት እውነተኛ አቅም ነው፡፡

4. በጣም ተጠያቂ ትሆናለህ፡፡

5. ለውጤታማ ደቀመዝሙርነት ራስህን ምሳሌ ስታደርግ ለክርስቶስ ለመታዘዝ የበለጠ የተሰጠህ እንድትሆን ይረዳሃል፡፡

6. ጠንካራ ክርስቲያናዊ ግንኙነቶችን ለማዳበር እድሉን ታገኛለህ፡፡

7. የዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ የስልጠና ጊዜያችንን መርህ ግብር እንደአስፈላጊነቱ ለመለዋወጥ ይረዳል፡፡

***የዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ግቦች***

1. ከእግዚአብሔር ጋር ባለህ ግንኙነት እና ኃይሉንም ለመለማመድ እንድታድግ መርዳት፡፡ (ኤፌሶን 3÷16-17)

2. የእግዚአብሔር ቃል ጥልቅ መረዳትህንና ለማጐልበትና የፀሎት ህይወትህን እንድታጠነክር መረዳት፡፡ (መዝሙር 1÷2-3 ፤ ቈላስያስ 4÷2)

3. ከሌሎች ጋር ጠንካራ ክርስቲያናዊ ግንኙነቶችን እንድታዳብር መረዳት፡፡ (1 ተሰሎንቄ 3÷12)

4. የክርስትናን ህይወት በማስመልከት ያሉህን ጥያቄዎች እንዲመለሱ መረዳት፡፡ (የሐዋርያት ስራ 17÷11)

5. ለህይወትህ ጥሩ መሠረት እንድታገኝና እንዴት ለሌላ ሰው ማስተላለፍ እንደምትችል በማስተማር መረዳት፡፡ (2 ቆሮንቶስ 5÷18)

***በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ ስልጠና እንድካተት ከኔ የሚጠበቁት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?***

1. ከክርስቶስ ጋር ያለህን ግንኙት ለማሳደግ መፈለግ፡፡

2. ለመማር የሚፈልግ አመለካከት - ከሌሎች ለመማርና ለመገናኘት ፍቃደኛ መሆን፡፡

3. ሳምንታዊ ክፍለጊዜዎች ለመካፈል መሰጠትና የስልጠና መምሪያ መፅሐፍቶችን ለመግዛት መሰጠት፡፡

4. የሚታዘዙ ስራዎችን ለማጠናቀቅ መሰጠት፡፡

**በዚህ ውሰጥ ለመሳተፍ፣ ይህንን መሰጠት በፀሎት ከግምት ውስጥ ታስገባለህ?**

ለመልስህ በ __________________________________ መልሼ እደውላለሁ /አገኝሃለሁ/

# ዳይናሚክ

## ---መሠረታዊ---

### *የመሪዎች መምሪያ*

እንድ አዲስ ክርስቲያን እምነትህንና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያለውን ምልልስህን ለማፅናት ቸሮታ ያለው ዕድል አግኝተሃል። አዲስ ህይወት ሲጀምሩ፣ ወደ ብስለት እያደጉ ሲመጡ እና የክርስቶስ ኢየሱስ እውነተኛ ደቀመዝሙር ሲሆኑ የማየት ደስታ ይኖርኃል። ይህ ካሉህ አገልግሎቶች በጣም አስፈላጊ ከሆኑት አንዱ ነው፣ ምክንያቱም የታላቁ ተልዕኮ ዋና ትኩረት ስለሆነ ነው። በማቴዎስ 28÷18-20 ***«ሂዱና ደቀመዛሙርቶ አድርጓቸው»*** ተብለናል። እንዴት ደቀመዝሙር ማድረግ እንዳለብን ሲቀጥል ***«ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው»*** ክርስቶስ እራሱ አገልግሎትህን ስልጣን ሰጥቶታል ደግሞም በኃይል ሊያስታጥቅ በዚያ እንደሚሆን ቃል ገብቶልኋል።

ኃዋርያው ጳውሎስ ይሄንን በቈላስይስ 1÷28-29 ገልፆታል።

> ***«እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍፁም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤ እኔም በብርታት በውስጤ በሚሠራው በእርሱ ኃይል ሁሉ እየታገልሁ ለዚህ ዐላማ እጥራለሁ።»***

የኛ ድርሻ ደቀመዝሙራችንን ለማስተማርና ለማሰልጠን መትጋት ነው። የእግዚአብሔር ድርሻ ደግሞ እኛን በኃይል ማስታጠቅና ደቀመዛሙርቱ እንዲያድጉ ማድረግ ነው። እኛ የራሳችንን ድርሻ ስንወጣ እርሱ እኛን ይጠቀማል።

### ለውጤታማ ክትትል ግቦች

ለመፈፀም /ለመተግበር/ ተስፋ የምታደርገውን ነገር በግልፅ ከተገነዘብክ ከአዲሱ ክርስቲያን ጋር በሚኖርህ የአብሮነት ጊዜ ውጤታማ ትሆናለህ።
**የእነዚህ አራት ክፍለ ጊዜዎች ዓላማ፦**

1. የእግዚአብሔር ቃል እንድንኖረበት የሚያስተምረንን መሠረታዊ እውነቶች ግለሰቡ እንዲገነዘብ ለመረዳት።
2. ግለሰቡን በእግዚአብሔር ቃል ላይ እምነቱን እንዲጥልና በእግዚአብሔር መርህ እንዲኖር በማስተማር ለመርዳት።
3. ግለሰቡ ከአንተ ጋርና ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ወዳጅነትን እንዲያዳብር ለመርዳት።
4. ግለሰቡን በዳይናሚክ መሠረታዊ ሌሎች ሰዎችን ማሰልጠን ሲጀምሩ ወደ ብስለትና ለጌታ ውጤታማ አገልግሎት ወደሚሰጡበት ሁኔታ ለማስገባት።



### *የመጀመሪያ ቀጠሮህን መወሰን*

ወንጌሉን የመሰበክና አንድን ሰው ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኙ እንዲቀበል የመርዳት እድሉ ከነበረህ ወይም የአንድ እንድትከታተለው ያለ ሰው ስም ከተሰጠህ፤ እንደ አዲስ ክርስቲያን አንድ ጓደኛህ እንዴት እንደረዳህ አካፍል። እንዲያድጉ ለመረዳት ፍቀድ። እንዲህ ማለት ትችላለህ፣ **«ይህንን ውሳኔ በማድረግህ በጣም ደስ ብሎኛል። አሁን አዲሱ ህይወትህን በሙላት መማርህ አስፈላጊ ነው። የተወሰኑ ጥቂት ቀናት አብረን በክርስቶስ ውስጥ ባለ በአዲሱ ህይወት እንዴት መኖር እንዳለብህ ለመማር ብንገናኝ ፍቃደኛ ነህ?»**

ከተስማሙ፣ ለመገናኘት የተለየ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ ወስኑ። ለክትትል የማይመቻቸው /የማይገኙ/ ከሆነ በህይወት ቡድንህ ወይም በሌላ በቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉ ሞክር። የእነርሱን ውሳኔ እንድትከታተላቸው ስማቸውን ለሰጠህ ሰው አሳውቅ። ወዳጃቸው ሁን። በመደበኛነት ፀልይላቸው።

### *መልካም ግንኙነትን ማዳበር*

በውጤታማ ክትትል ውስጥ ያለ በጣም አስፈላጊ ነገር የምታዳብረው ግንኙነት ነው።

**እንደ መልካም ወዳጅ፦**

1. በደቀመዝሙርህ ፍላጐት እንዳለህ አሳይ
   - ሁልግዜ ስማቸውን ተጠቀም፣ እያቸውና ፈገግ በል።
   - ስለህይወታቸው ስለፍላጐታቸው ጠይቅ።
   - አዳምጥ። በሚያናግሩህ ጊዜ ደስ እያለህ መልስላቸው
   - እነርሱን የሚያሳስባቸውን ነገር ለይ።
   - ከተቻለ ፍላጐታቸውን ለማሟላት መገኘት
   - ለህይወታቸው ኢየሱስ እንዴት አግባብ እንደሆነ አካፍላቸው።
   - በድርጊታቸው ሳይሆን ከፍቅር የተነሳ ተቀበላቸው።
   - ስለሚያውቁት አዲስ እውነት በአድናቆት ተሞላ።
   - ለማንኛውም ጥያቄ ወይም መልስ አለመስማማትን በጭራሽ አታሳይ
   - ስለሌሎች በጎውን ተናገር።

2. ለደቀመዝሙርህ ህይወትህን አካፍል

- ኢየሱስ እንዴት በህይወትህ አግባብ እንደሆነ አካፍል።
- በሁሉ ነገር መልካም ምሳሌ ሁን
- ስለሚያስፈልጉህ ነገሮች ግልፅ ሁን
- እንዴት የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ እንደምታደርግ ለማካፈል ግልፅ ሁን።
- መመለስ ካልቻልክ አላውቅም በል። በአንድነት መልሱን ለማግኘት መሞከር
- በእግዚአብሔር ላይ ያለህን መተማመን አሳይ።
- ትጉ ሁን።
- ወዳጅ ሁን
- ከክትትል ሰዓታችሁ ውጪ በአንድነት ጊዜ አሳልፉ። ሁለታችሁም የምትወዱትን ነገር አድርጉ።
- ለደቀመዝሙር ሁልጊዜ በመደበኛው ፀልይ።

## የክትትል ክፍለ ግዜህ

1. አመቺና ከረብሻ ነፃ የሆነ ቦታ መምረጥ

2. እርስ በእርስ ሰላምታ መለዋወጥ። በመጀመሪያ ግንኙነታቸው ለመተዋወቅ ጊዜ ውሰዱ። ስለቤተሰብ፣ ስለሙያ ወ.ዘ.ተ ጠይቅ። በእያንዳንዷ ሳምንት በህይወታቸው ፍላጐት እንዳለህ ለማሳየት ጊዜ ውስድ። ለጥናቱ 30 ደቂቃ መተውህን እርግጠኛ ሁን።

3. ወደ መጀመሪያው ክፍለ ጊዜ እንዲህ በማለት ተሸጋገር፣ «እርስ በእርስ ለመገናኘትና ለመተዋወቅ በመቻላችን ደስ ብሎኛል። እንደ አዲስ ክርስቲያን ልንማራቸው ባሉት ነገሮች ደስ ይልሃል። እነዚህ ወረቀቶች ስለ ወሳኝ ጉዳዮች እንድንነጋገር ይረዱናል።» ለሚከተሉት ክፍለ ጊዜዎች ርዕስ ጉዳዮን እንዲ በማለት አስተዋውቅ፣ «በዚህ ሳምንት (ርዕሱን ማንበብ) እናጠናለን።» ስለ እያንዳንዱ ክፍለ ግዜ ያለህን አድናቆት አካፍል።

4. በየሳምንቱ ለደቀመዝሙርህ ያጠናቀቅኸውንና አዲሱን ክፍል አቅርብ።



5. የክፍሉን እያንዳንዱን ነጥብ ተወያይ።
   ሀ. ትምህርቱንና የመፅሀፍ ቅዱስ ቁጥሮችን እየገለጡ ማንበብ። በቅንፍ ውስጥ ያሉ ቁጥሮች ስለተሰጠው ነጥብ ጥያቄ ሲኖራቸው ብቻ መነበብ ይኖርባቸዋል።
   ለ. በአንደኛው ክፍል ምናልባት የራስህን መፅሐፍ ቅዱስ ታጋራ ይሆናል ነገር ግን በእያንዳንድ ክፍለ ግዜ ደቀመዝሙርህ መፅሐፍ ቅዱስ ይዞ እንዲመጣ አበረታታው።መፅሀፍ ቅዱስ የሌላቸው ከሆነ የራሳቸው የሆነ አንድ ያገኙ ዘንድ ሁኔታዎችንን በማመቻቸት መርዳት። በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መፅሐፍት ደቀመዝሙርህ እንዲያውቃቸው እርዳው። ማውጫውን ማሳየትና እንዴት መፅሐፍ ቅድስ በመፅሐፍት፣በምዕራፍና በቁጥሮች እንደተከፋፈሉ አሳያቸው። ትዕግስት ይኑርህ፣ ከተቻለ በራሳቸው ቁጥሮቹን ይፈልጉ።
   ሐ.በተጨማሪ ጥያቄዎች ውይይቶችን ማነሳሳት፡-
   - በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሌላ ምን ታያለህ?
   - ኢየሱስ ይህንን ሲል ምራ እንደሆነ ታስባለህ?
   - በራስህ ቃላት ይህንን እንዴት ትገልፀዋለህ?
   - ዛሬ እንዴት ነው ይሄ እኛን የሚነካን?
   - በዚህ ክፍል ውስጥ ስለራስህ አንድ ነገር ተማርክ?

**በራስህ**

በእያንዳንዱ ክፍል ግዜ የተማራቸውን መፅሀፍ ቅዱስ መርህዎች ለማጠናከር ደቀመዝሙርህን በቤት ውስጥ የሚሰራውን አጭርና ግልፅ እንቅስቃሴዎች እንዲያከናውን አበረታታው።

**ቁጥሮችን በቃልህ ያዝ**

የእግዚአብሔር ቃል በልባቸው ውስጥ የመያዛቸውን አስፈላጊነት አፅንኦት ስጥ በሚቀጥለው ክፍለ ግዜ በቃላቸው ላንተ ደግመው እንደሚናገሩ ይወቁ።

***መዝጊያ***

ለሚቀጥለው ግንኙነት በክፍል 1፣2 እና 3 መጨረሻ ላይ ጊዜውን መመደብ በክፍል 3 መጨረሻ ላይ ደቀመዝሙርህ **«የህይወት ታሪኬን መናገር»** የተሰኘውን ቅፅ በመጠቀም ወደ ክርስቶስ የመጣበትን ልምምዱን ለማካፈል አዘጋጀው። ታሪካቸውን ለአንድ ጓደኛቸው ያካፍሉ ዘንድ እድሉን አመቻችላቸው። ጓደኞቻቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ከተቀበሉ ከደቀመዝሙርህ ጋር የዳይናሚክ መሠረታዊ ክፍል አንድን ሲጀምር መገናኘት ያስፈልግሃል። ደቀመዝሙርህ በራሳቸው ወደ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ ከመሄዳቸው በፊት ዳይናሚክ መሠረታዊን ለአንድ ሰው ለማስተላለፍ መጀመር ይኖርባቸዋል።

በክፍል 4 መጨረሻ ላይ «ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ - አንድ መልካም ዕድል» የተሰኘውን ክፍል አንብብና ወደ ዳይናሚክ ደቀመዘሙር ማድረግ እንዲሄዱ አነሳሳቸው። ከአንድ አዲስ ደቀመዝሙር አድራጊ ጋር እንዲገናኙ መውሰድ ወይም ለእነርሱ ልታዘጋጅላቸው ትችላለህ። ክፍል አራትን እንደተጠናቀቀ የምስክር ወረቀቱን ስጥ። የሚመች ከሆነ፣ ይህንን አሰጣጥ በህይወት ቡድንህ (ትንሹ ቡድን) ላይ አድርግ።

**በፀሎት ዝጋ።**

# የምስክር ወረቀት

ይህ የምስክር ወረቀት

ለ፡ ____________________

## *ዳይናሚክ መሰረታዊ*

ስልጠናን በሚገባ ስላጠናቀቁ ተሰጥቷቸዋል፡፡

ቀን ____________

____________

የስልጠናው ዳይሬክተ